ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

**በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ**
**መስከረም 12 ቀን 2008 ዓ.ም. የተላለፈ**

## ቅጥ - አምባሩ የጠፋበት ትግል ፤
## እየዳከረ ይቀራል !

የትግል መሠረታዊ ምክንያት ፤ ሕዝብን ከጨቋኝ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት መሆኑ ባይዘነጋም ፤ በግል ደረጃ፤ መጀመሪያ ራስን ነፃ ሳያወጡ፤ ሀገርንና ሕዝብን ነፃ አወጣለሁ ማለት ዘበት ነው። ራስን ማታለልና ሕዝብንም መደለል ይሆናል ። ሰው ራሱን እያተለለ ለመኖር ከፈለገ፤ የግል ጉዳዩና ፍላጎቱ በመሆኑ፤ የራሱ መብት ነው ተብሎ ይታለፍለታል። ሕዝብን እያተለለና እያጭበረበረ ግን ሊኖር አይችልም። አይገባውም ። አይፈቀድለትምም ።

በተለይ በትግል ስም ፤ የግል ዝናን ለማራመድና፤ ሃብትና ንብረት ለማካበት የሚደረግ ጥረት ሁሉ ፍሬ-ቢስ ከመሆን አያልፍም። የብዙሃኑን ፍላጎትና ጥቅም ይፃረራልና። ይህም ሃቅ፤ ባለፉት አምሳ ዓመታት፤ በሀገራችን የትግል ታሪክ ብዙ ማስረጃዎችን የሚያስጠቅስ ክስተት አስቀምጦ አልፏል። ለሥልጣን መቋመጥ፤ አለትን መቧጠጥ መሆኑ፤ በግልጽ ታይቷል። በአለፈው ግማሽ - ምዕተ-ዓመት ፤ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ፤ ለቁጥር የሚያስቸግሩ ድርጅቶችና ስብስቦች እንደ እንጉዳይ እየፈሉ ከስመዋል። የታሪክ አሻራ ስላልነበራቸው፤ ደብዛቸው እንደ ሎጥ ሚስት የዶግ-አመድ ሆኖ ቀርቷል። አጀማመራቸው ቅጥ- ያጣ ስለነበር፤ አጠፋፋቸውም፤ እንዳዚሁ፤ ቅጥ-ያጣ እየሆነ ተሰውሯል። አብዛኛው ሀረግ-ሬሳ ስለነበረ፤ እራሱን ችሎ፤ ሀይወት ዘርቶ መቀጠል ሳይችል ቀርቷል ። ይህም፤ የግል ነፃነት ከማጣት የመጣ ስንኩልነት ነው።

ለተበደለ ሕዝብ መቆርቆርና መታገል፤ የሚያኮራና የሚያስመሰግን ዓላማ ነው። ለዚህ የተቀደሰ ዓላማ መሥዋዕት መክፈል ደግሞ፤ የበለጠ አስመስጋኝና አኩሪ ታሪክ ሆኖ ይኖራል። ከሁሉ አስቀድሞ ግን ፤ ሕዝብን ነፃ ለማውጣት ከመታገል በፊት፤ ራስን ነፃ ማውጣት ወሳኝ ይሆናል ። ራሱን ነፃ ያላወጣ ፤ ለራሱም ይሁን ለድርጅት፤ ለሕዝብም ይሁን ለሀገር ጠቃሚ ሊሆን አይችልም። ነፃ አውጭ ነኝ ብሎ የሚያምን ሰው፤ በቅድሚያ ራሱን ነፃ ማውጣቱን ለማረጋገጥ ከፈለገ፤ የሚከተሉት ባኅርያት እንዲኖሩት ይጠበቅበታል ።

1. የራሱ ተገዥ እንጅ፤ ጭንቅላቱን ለሌሎች በተለይም ደግሞ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት ለሆኑ ባዕዳን ሊያስገዛ አይገባውም ። ይህንን ባኅርይ ለማግኘት ደግሞ፤ በራስ መተማመንን ይጠይቃል።

2. ማንም ሊጠይቀው የማይችል ተክለ-ስብዕና እንዲኖረው ይጠበቅበታል ። እንዲያውም፤ የእኔን ተክለ-ስብዕና ጥያቄ ውስጥ ሊያስገባ የሚችል ሰው፤ ገና በሀገሪቱ አልተፈጠረም እስከ ማለት የሚያስችል በራስ የመተማመን ችሎታ እንዲኖረው ያስፈልጋል ። ይህ አባባል፤ በትዕቢት የተወጠረ አነጋገር ሳይሆን፤ ነፃ አስተሳስብን ለመግለፅ የተቃጣ የማንነት ስብዕና መግለጫ ነው ።

3. ፍፁም ይሆነ የሞራል ዕሴትና ምግባረ- ሰናይን አንግቦ መታገል፤ የሌሎችን ድፍረትና ጥቃት ለመቋቋም ያስችለዋል። አጉራ-ዘለል የሆነ እርምጃ ከመውሰድም ይታቀባል ። ይልቁንም፤

" ያም አለ፤ ያም አለ የአተር ገለባ ነው፤

ያልሆነ ተናግሮ ማጣፊያ ሚ'ቸግረው። " በማለት ለአሉ-ባልታ ዋጋ አይሰጠውም ።

እንዲያውም፤

" ለማይጎዳ ጠላት ማገስ ይጨነቃል፤

ማማት የለመደ ዉሃ ያላምጣል ። "

በማለት፤ ክብሩን ጠብቆ ራሱን አያስከበረ ትግሉን ይቀጥላል ።

4. ማንም ዜጋ በግለሰብ ደረጃም ሆነ በቡድን ተቧድኖና ድርጅት ገንብቶ ዕንባ ጠባቂና የሀገር ጥቃት ተከላካይ ሊሆን የሚችለው፤ ምግባሩን ከተግባሩ፤ ጋር አዛምዶ መታገል የሚችል መሆኑን ሲያረጋግጥ ነው። በሙስና የተነከሩ የፖለቲካ ታጋዮችንና በዓለማዊ ኑሮ የተዘፈቁ የሃይማኖት መሪዎች ሀገርን ምንኛ እንደሚጎዱ ጠንቅቆ ያውቃል። ባይጠላቸውም፤ እየናቀ አጥብቆ ይቃወማቸዋል። የሚቃወማቸውም፤ ለሀገርና ለሕዝብ ጥቅም ጎጅዎች በመሆናቸው ብቻ ነው።

5. ኢትዮጵያ ዛሬ፤ ማንም ተንስቶ በክብሪት ቢለኩሳት፤ በቀላሉ የምትጋይ ሀገር መሆኗን ጠንቅቆ ስለሚረዳ፤ ይህ እንዳይከሰት አጥብቆ ይጨነቃል። እሳቱ ከየትኛውም አቅጣጫ ይምጣ፤ በሁኔታው ተጠቃሚ የሚሆኑት ወያኔና የሀገራችንን ጥፋት የሚመኙ የኢትዮጵያ ጠላቶች ብቻ ናቸው። ዕዳውና መከራው የሚተርፈው ግን ያው ብዙሃን ለሆኑት ለአሳረኛው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሆኖ ይቀራል ።

የመርኮቶና የአራዳ ጩሊሌዎች የሚነፉት ፊሽካ ከአንድ ሰሞን ያለፈ ሆይ ሆይታና ከጊዚያዊ ውቂው-ደብልቂው ግርግር በላይ አይዘልቅም። ከወቅታዊው የፕሮፓጋንዳ ፍጆታ በላይ ማሰብ፤ ቀጣይነት ያለው ትግል ለማካሄድ የማይጠቅም መሆኑን መገንዘቡም ጠቃሚ ነው።

6. ሀገሪቱ የተመሰረተችበትን ዋልታ የሚያናጋ ተግባር እያካሄዱ፤ ሀገር እንጠቅማለን ማለት፤ እርስ በእርሱ የሚጋጭ በመሆኑ፤ በኢትዮጵያዊነቱ የሚተማመን ታጋይ፤ ከእንደዚህ ዓይነቱ ተግባር ራሱን ነፃ

ያደርጋል ። ሀገር እያስቆረሱ፤ ሕዝብ እየበተኑ፤ ታሪክ እያወደሙ፤ ባኅል እያረከሱ፤ ኢትዮጵያን መታደግ የሚባለው ወያኔያዊ ቀልድ ነው ። ገድሎ እግዚአብሔር ይማርህ ማለትስ እንዴት ይቻላል ?

የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ወዳጅ ጠላቱን የሚያውቅ ሕዝብ ነው። " እንኳን ሲሸጡት፤ ሲስማሙበትም " በሚገባ ያውቃል። ይረዳል። ከኢትዮጵያዊያን ፍላጎትና ጥቅም ውጪ ከባዕዳን የሚለገስ እርዳታ ኢትዮጵያን ለማዳን ተፈጥሮው አይፈቅድለትም ። ይልቁንም፤ ወያኔ በኢትዮጵያ ውስጥ፤ አሉባልታን በፕሮፓጋንዳ ፤ ዕልቂትን በጦር ሜዳ ከማካሄድ የሚመለስ እንዳልሆነ በተግባር ላለፉት 24 አመታት ያስመሰከረ ኬይሲና ጎጠኛ ቡድን ነው። አንድ ነገር ግን ለማስገንዘብ ግድ ይለናል። ይኸውም ሀገራችን ኢትዮጵያ፤ በተጠመደ ቦምብ የተከበበች ሀገር ፤ ሕዝቧም፤ በስለላ ሽረሪት/ መረብ የተጠለፈ ዜጋ መሆኑና ይህንን ሁኔታ በሚገባ የሚጠቀሙ ባእዳን ያ እኖራቸውን መዋቅ ነው ። ይህንን መቋቋም የሀገር ወዳድ ዜጋና ኃይል እንደሆነ ደግሞ መግለፁ አግባብነት አለው።

ከዚህ በቀር፤ ወያኔዎቹ፤ ለአገዛዛቸው እጅግ አደገኛ ናቸው በሚሏቸው በወሎ-፤ በጎንደርና በጎጃም አካባቢዎች፤ የአድባሩና አውጋሩ ባላባት የሆኑ አዛውንትን አጥፍተዋቸዋል። የዚህ ርምጃ ምክንያት ለታሪክ ምስክርነት ሊጠቅሱ የሚችሉትን ሁሉ ደብዛ ለማሳጣት እንደሆነ ለማንም ግልፅ ነው ። የንጹሃንን ደም ማፍሰስ፤ ሰበቡ፤ ዉሎ አድሮ በራስ ላይ እንደሚደርስ ግን አልተገነዘቡትም ። ቢያንስ ቢያንስ፤ ደምን፤ ደም እንደሚያደርቀው ሊያውቁት በተገባቸው ነበር።

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ዕንባውን ጨርሶ የቀረው ቢኖር ደሙ ብቻ ነው። ማልቀስ ደግሞ ሀዘኔታን ለመግለፅ ይረዳ ይሆን እንጂ፤ ፍቱህ መድሃኒትን አያስገኝም። ስለሆነም ለሰብዓዊ መብቱ ፤ ለነፃነቱና ለሀገሩ፤ ዋጋ ሊከፍል የሚችለውም፤ ያው የቀረውን ደሙን ብቻ ነው። በታሪኩም፤ ለነፃነቱና ለሀገሩ ሉዓላዊነት ሲል የደም መሥዋዕት ሲከፍል እንደኖረ፤ ከወያኔ በስተቀር፤ ሌሎች ጠላቶች ሳይቀሩ እንኳ የሚመሰክሩት ሃቅ ነው።

የሰው ልጅ በገሃነም ወስጥ ቢወድቅም፤ ገነትን መመኘቱ አይቀርምና፤ የኢትዮጵያ ሕዝብም፤ ከወደቀበት የዘረኛ አገዛዝ መላቀቁ አይቀርም ። ይህ ደግሞ በባዶ ተስፋ ላይ የተመሰረተ ምኞት ሳይሆን፤ በተጨባጭ ነግ ተነገ ወዲያ የሚረጋገጥ ዕውነታ ይሆናል ።

ለማጠቃለል፤ ቅጥ- አምባሩ የጠፋበት ትግል ነፍስ ዘርቶ ያመረቃ ውጤት እንዲያስገኝ ከተፈለገ ፤ የሚከተሉትን ጉዳዮች ተግባራዊ ሊሆኑ ይገባል፦

1ኛ. መጀመሪያ በትግል ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ዜጋ በቅድሚያ ራሱን ነፃ ማውጣት አለበት። እራሱን ነፃ ያላወጣ ትግል/ ታጋይ፤ ሀገርና ሕዝብን ነፃ ሊያወጣ አይችልም ። እርስ በእርስ ከመጠላለፍና ከመከፋፈል ራሱን ማጽዳት የመጀመሪያው ሂደት ሊሆን ይገባል። ራሱን ነፃ ያወጣን ዜጋ ከመሰሎቹ ጋራ የራሱን ነፃ ድርጅት ገንብቶና የድርጅት ነፃነቱን ጠብቆ መታገል ፤ የማንነቱ መግለጫ መሆኑን ሊገነዘብ ግድ ይለዋል።

2ኛ. በዓላማ አንድነት ዙሪያ መሰባሰብ አልፋ-ኦሜጋ ነው። የዓላማ አንድነት አላቸው ሲባል፤ በሀገር/ ህዝብ አንድነትና ነፃነት የሚያምኑ ወገኖች ማለት ነው። እኛ በበኩላችን፤ ሀገር ከሚገነጣጥሉ፤ ሕዝብ ከሚከፋፍሉ ድርጅቶች ጋር ጉዳይ የለንም፡፡ ሲያልፉም አይነኩንም!

3ኛ. የተለየዩ የትግል ስልቶች ያላቸው ድርጅቶች፤ ሊያቀራርባቸው በሚያስችላቸው ሁኔታዎች/ ዘዴዎች ተወያይተው አንድ ዓይነት ስምምነት ላይ ሊደርሱ ይጠበቅባቸዋል ። የጋራ እምነትና መተማመንንም መፍጠሩ የማያልፉት ግዴታቸው መሆኑን መገንዘብ ጠቀሜታው የጎላ ነው። ያለፉት 24 ዓመታት እንደሚያረጋግጡት በየፊና መሰለፍና መታገል የተቃዋሚውን ጎራ እንዳይጠነከር ዓይነተኛ ምክንያት እንደሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ በማያሻማ መንገድ ተረድቶታል። ሁሉም ናቸው ባይባልም ፤ አብዛኛዎቹ ድርጅቶች ከወያኔ ስለላ መርብ የነፁ ናቸው ማለት አይቻልም። የወያኔ ስለላ መረብ፤ እንኳንስ በተቃዋሚዎች ቀርቶ ፤ በቤተክርስቲያናት ሳይቀር በመግባት እያመሰ ለመሆኑ የአደባባይ ምሥጢር ሆኗል ። " ዝርዝር ኪስ ይቀድዳል " ነዋና ወደ ዝርዝር መግባት አስፈላጊ አልሆነም ።

4ኛ. የኃይል አሰላለፉን በማያሻማና በግልፅ ለይቶ ፤ ሚዛኑን ማስቀመጥ ጊዜ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር አይደለም። በመሆኑም የወያኔና አገዛዝ ከነግሳንግሱ ለማስወገድ ይቻል ዘንድ፡-

ሀ . በኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና የዜጎቿ ዕኩለነት አምነው የተደራጁ ድርጅቶችና ተቋማት በአንድ ላይ ተጠራርተው፤ ተወያይተው አንድ ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ የሀገሪቱ ሁኔታ ከምን ጊዜውም በላይ አገስዳጅ እየሆነ መጥቷል ።

ሐ. እነኝህ ኃይሎች የሚገነቡት ሀገራዊ አንድነት ኃይል በቀላሉ የሚበገር አይሆንም። ይህ እንዳይፈጠር፤ የኢትዮጵያ ጠላቶች ሌት-ከቀን ተግተው ይሰራሉ። የጠላትን ሴራ አክሽፎ ሀገራዊ የአንድነት ኃይል መፍጠር የሁሉም ቀዳማይ አጀንዳ ሊሆን ይገባል።

5. ትግሉን አሁን ካለበት አቅጣጫ-ቢስ  አካሄድ ማውጣት ከተቻለ፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ አንድ ዕመርታ ማሳየት ይቻላል ብለን እናምናለን።  ለዚህ ተግባራዊነት መሳካት ለሁሉም ጥሪያችንን አናስተላልፋለን  !

ኢትዮጵያ በሕዝቧ ተከብራ ትኖራለች !!